# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 172 ነሃሴ 26 2003 ገጽ 1


**በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ "የኔ ተሳትፎ ኢምንት ነው" ሳይል በተቻለው ሁሉ ትግሉን የሚያግዝበት ወቅት ላይ ደርሰናል። የእያንዳንዳችንን ትናንሽ ተሳትፎዎችንም እያቀናጀን በማጎልበት ወደህዝባዊ ማዕበልነት ማድረስ የሁላችንም ሥራ ነው። ትናንሽ ነውጦች ሲጠራቀሙ ታላቁን ማዕበል ያስነሳሉ ብሎ ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል።**

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ

## የአለም የገንዘብ ተቋም ኢትዮጵያን ያልታደለች ሃገር ሲል ገለጸ፣ በሃገሪቱ ሁኔታዎች ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሱ ነው አለ

በምህጻረ ቃሉ አይ ኤም ኤፍ በመባል የሚታወቀው የአለም የገንዘብ ተቋም የወያኔው ዘረኛ አገዛዝ ፖሊሲ የፈጠረው የዋጋ ግሽበት ከቁጥጥሩ ውጭ እየሆነ በመምጣቱ ኢትዮጵያን ያልታደለች ሃገር ሲል የገለጸ ሲሆን፣ በሃገሪቱ ሁኔታዎች ከመሻሻል ይልቅ እየተባባሱ መምጣታቸውን ባወጣው ሪፖርት ላይ ገልጹአል።

ለወያኔ ቅርበት እንዳልዉ የሚታወቅለት የሪፖርተር ጋዜጣ በ ዋሽንግተን ዲሲ የሚገኙ የዓለም ባንክ የዉስጥ ምንጮቹን ዋቢ በማድረግ እ.ኤ.አ ከኅዳር 2010 ዓ.ም. ጀምሮ የኢትዮጵያ ማክሮ ኢኮኖሚ አፈጻጸም ሚዛኑን እየሳተና እየተበላሸ መምጣቱን በማሳሰብ አይኤምኤፍ የወያኔን አገዛዝ ከፉኛ የሚያወግዝ ሪፖርት ማዝጋጀቱን አጋለጠ ፡፡ ሪፖርቱ ጠንካራ ቃላትንም በመጠቀም ዘረኛዉን የወያኔን አገዛዝ በተጠያቂነት ከፉኛ የተቸ መሆኑ፣ ብስጭት የፈጠረበት የመለስ አገዛዝ ሪፖርቱ ለአባል አገሮችና ለሕዝብ በኢንተርኔት እንዳይሰራጭ ያገደ መሆኑንም ገልጹአል፡፡

ይሕ ለህዝብ ይፋ እንዳይደረግ በወያኔ ታገደዉ የአይኤምኤፍ ሪፖረት ባሁኑ ሰዓት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ጉዳይ አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንዳለና ለዚህም በዋናነት ምክንያት ነዉ ያለዉ ካለፉት ሁለት ዓመት ወዲህ እየጨመረ የመጣወንና ባሁኑ ጊዜ 40% የደርሰዉን የዋጋ ግሽበትን ነዉ።- ለዋጋ ግሽበቱም መባባስና አሁን ካለበት ደረጅ ያደረሰዉ፣ የባንክ የወለድ ምጣኔ ከዋጋ ግሽበት በታች መሆኑ (Highly Negative Real Interest Rate)፣ ከዚህ በተጨማሪ የወያኔ ልማት ድርጅት ተብዬዎች በርካሽ ወለድ ከባንኮች የሚበደሩት ብዛት ያለው ገንዘብ መሆኑን በሪፖርቱ ውስጥ አካቷል፡፡ የኢትዮጵያ የዋጋ ግሽበት ከኬንያ፣ ከኡጋንዳ፣ ከታንዛኒያና ከሰሀራ በታች ካሉ አገሮች የዋጋ ግሽበት ጋር ሲነፃፀር በአራት እጅ እንደሚበልጥ አይኤምኤፍ በሪፖርቱ ጠቅሷል፡፡ (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዊኪ ሊክስ ባለፈው ሳምንት ይፋ ባደረገው ምስጥራዊ ማስረጃ ወያኔ ህግ አድርጎ ያወጣው "የፀረ ሽብርተኝነት" አዋጅ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ለመወንጀል በሥራ ላይ እንዳማይውል ለአሜሪካ መንግሥት ተገልጾ እንደነበር ይፋ ሆነ

የአሜሪካ ውጪጉዳይ ሚንስቴር በተለያዩ አገሮች ከሚሠሩ ዲፕሎማቶቹ ያሰባሰባቸውን ምስጥራዊ ሪፖርቶች ለህዝብ እይታ በማቅረብ ላይ የሚገኘው ዊኪሊክስ በመባል የሚታወቀው የመረጃ ድረገጽ፤ ባለፈው ሳምንት ሃሙስ እንደፈረንጆች አቆጣጠር ኦገስት 25 2011 ያሰራጨው መረጃ፤ ወያኔ ተቃዋሚዎቹን ለማስፈራራት ህግ አድርጎ ያወጣው "የጸረሽብርተኛነት" አዋጅ በፓርላማ ተብዬው የወያኔ ሸንጎ ከመጽደቁ በፊት አዲስ አበባ ለሚገኘው የአሜርካ ኤምባሲ ቀርቦ መግለጫ እንደነበር አመለከተ።

ዊኪ ሊኪስ ይፋ ባደረገው በዚህ መረጃ ስለ የጸረሽብር ረቂቅ አዋጁ ለወቅቱ የአሜሪካ አምባሳደረ አምባስደር ያማማቶ ማብራሪያ ለመስጠት የተላከው ዘረኛው መለስ ዜናዊ በጊዜያዊ ጥቅምና የሥልጣን ትርፍራፊ የራሱ ጄሌ ካደረጋቸው አንዱ የሆነው ብርሃኑ አዴሎ እንደሆነ ተገልጾአል። ብርሃኑ አዴሎ በመለስ ዜናዊ ጽ|ቤት ሃላፊና በምንስትርነት ማዕረግ የካቢኔ ሹም እንደነበር የገለጸው የአሜሪካ ኤምባሲ መልዕክት፤ የጸረ ሽብር አዋጁን ጨምሮ ከምርጫ 97 ወዲህ በአገሪቱ ውስጥ የታወጁትን ሌሎች ተመሳሳይ አፋኝ ህጎች በሙሉ በማርቀቁ ሥራ ብርሃኑ አዴሎ ዋና ተዋናይ እንደነበረ በሪፖርቱ አካቶታል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በንጹሃን ዜጎች ላይ የተያያዘውን የእስራት ዘመቻ ቀጥሉአል፣ በቅርቡ ሁለት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አካላትን አሰረ

ህዝብን በማፈንና በጠመንጃ ሃይል በማስፈራራት እየገዛሁ እኖራለሁ በሚል ከንቱ ቅዠት የተዋጠው ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በተለይም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በንጹሃን ዜጎች ላይ የጀመረውን እስራትና አፈና በተጠናከረ መልኩ በመቀጠል ሰሞኑን ሁለት የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አባላትን ማሰሩን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ ገለጸ። እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በዘረኛው አገዛዝ የታሰሩት ሁለቱ የተቃዋሚ ፓርቲ አመራር አካላት አንደኛው የኦሮሞ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ (ኦፌዲን)ምክትል ሊቀመንበርና የመድረክ ሥራ አስፈፃሚ የሆኑት አቶ በቀለ ገርባ ሲሆኑ ሌለው በፖሊስ ቁጥጥር ስር የዋሉት ደግሞ የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግረሱ(ኦብኮ) ፤ አቶ ኦልባና ሌሊሳ መሆናቸው ታውቁአል።

እንደ ዘጋቢያችን ሪፖርት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የእንግሊዝኛ ቋንቋ መምህር የሆኑት አቶ በቀለ ገርባ የታሰሩት፤ በቅርቡ በሽብርተኝነት ከተፈረጀው ከኦሮሞ ነፃነት ግንባር ጋር ግንኙነት አላቸው በሚል ሲሆን የኦሮሞ ብሄራዊ ኮንግረሱ(ኦብኮ) የአቶ ኦልባና ሌሊሳ ክስ፤ ከሽብርተኝነት ጋር የተያያዘ ይሁን አይሁን ፤እስካሁን የተገለፀ ነገር ነገር አለመኖሩን ለማወቅ ተቿሉአል።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት ጋር ቃለምልልስ ያደረጉት የኦሮሞ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ(ኦፌዲን) ዋና ፀሀፊ አቶ በቀለ ነገአ፤ የወያኔው አገዛዝ ሁለት የታቃዋሚ መሪዎችን በፈጠራ ክስ ማሰሩን በማውገዝ፤ የኢትዮጵያ ህዝብ በአንድነት በመነሳት ይህን አገዛዝ "በቃ!"ሊለው ይገባል ሲሉ ጥሪ ማቅረባችውን ዘግቡአል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ዘረኛው አገዛዝ ሲጠቀምባቸው የነበሩ ባለስልጣናትን ማስወገድ ቀጥሉአል፣ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አፈ-ጉባኤ ና ሎሎች የክልሉ ባለስልጣናት ተረኛዎች ሆነዋል

ለሚፈልገው አላማ መሳካት አንድ ወቅት ስልጣን ላይ ያስቀመጣቸውን ሆድ አደሮች እንደሸንኮራ አገዳ መጥጦ በመጣል የሚታወቀው የዘረኛ አገዛዝ ፤ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት አፈ ጉባዔ ሆኖ በመሥራት ላይ የሚገኘውን ሀብታሙ ኢካ ፈለቀ፣ በሙስና ወንጀል ወደ እስር ቤት ማስገባቱን ሪፖርተር በመባል የሚታወቀውና ለአገዛዙ ቅርበት ያለው ጋዜጣ ዘገበ፡፡

እንደ ሪፖርተር ዘገባ ሀብታሙ ኢካ በቁጥጥር ሥር የዋለው፤ የክልሉ ምክር ቤት ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ ያለመከሰስ መብቱ ከተነሳ በኋላ ሲሆን ከአፈ ጉባዔው ጋር የተጠረጠሩ በርካታ ባለሥልጣናትና ግለሰቦችም በቁጥጥር ሥር እየዋሉ እንደሆነ ታውቁአል፡፡

በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የአካባቢ ተወላጆችን በስልጣን ወምበር ላይ እንዲቀመጡና የሚፈልገውን እንዲፈጽሙ ሁኔታዎችን በማመቻቸት የሚታወቀው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናቱ ከቁጥጥር እንዳይወጡ አንገታቸውን ማስደፊያ የሚሆን እንደሙስና ባሉ ወንጀሎች እንዲዘፈቁ እንደሚያደርግና ባለስልጣናቱ አገልግሎታቸውን ሲያጠናቅቁ በወንጀል ወደ ዘብጥያ ሲያወርድ እንደቆየ በተደጋጋሚ ሲዘገብ መቆየቱ ይታወሳል፡፡

## በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነትና ስራ አጥነት ተባብሰዋል፣ የተፈጠሩት ችግሮች የዘረኛውን አገዛዝ ውድቀት ያፋጥናሉ ተባለ

ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ የመጣው የኑሮ ውድነት ከመቼውም ጊዜ በላይ አደገኛ ሁኔታ ላይ መድረሱና ለረጂም አመታት በትምህርት ላይ የቆዩ የድሃ ቤተሰብ ልጆች ስራ አጥነት እጂግ መስፋፋት የዘረኛውን አገዛዝ ውድቀት ሊያፋጥኑት እንደሚችሉ ዘጋቢያችን ያነጋገራቸው አስተያየት ሰጪዎች ገለጹ።
ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ዘገባ በያዝነው አመት ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርታቸውን አጠናቀዋል ተብለው የተመረቁ ወጣቶች ቁጥር እጅግ በጣም ብዙና በመቶ ሺሆች የሚቆጠር መሆኑን የገለጸ ሲሆን ቀደም ብሎ ትምህርታቸውን ከተለያዩ ተቋዋማት ያጠናቀቁ ወጣቶች ለአራትና አምስት አመታት ለስራ አጥነት በተዳረጉበት ሃገር፣ብሎም የስራ እድል ባልተፈጠረበት ሁኔታ ይህን ያህል ወጣት ተመራቂ መጨመሩ በሃገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ ቀውስና አመጽን ሊያስነሳ እንደሚችል ተመራቂ ተማሪዎች አስተያየታቸውን የሰጡት መሆኑን ገልጻኡአል።

ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በያዝነው አመት ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ ተማሪዎች ውስጥ የእንግሊዝኛ ቋአንቋአ ትምህርት የ2003 ዓም ምሩቅ የሆነች ስሙዋ እንዳይጠቀስ የጠየቀች ወጣት ወደፊት ተመራቂዎች ስለሚኖራቸው እጣ ፈንታ አስተያየት እንዲሰጣት ላቀረበላት ጥያቄ በሰጠቺው አስተያየት፣ "ቀደም ብለን ትምህርታችንን የጀመርን ምናልባት ፊደል በመቁጠራችን የተሻለ እድል ይኖረናል በሚል እምነት ነበር፣ ይሁን እንጂ አሁን በሚታየው ተጨባጭ ሁኔታ ላለፉት አራትና አምስት አመታት ስራ አጥ ሆነው የተቀመጡ ወጣት ተመራቂዎችን ባይናችን እያየን በመሆኑና የወደፊቱም የሃገሪቱዋ ወጣቶች እጣ ፈንታ ወደ ባሰ አዘቅት እያመራ በመሆኑ አንዱ እየተራበ፣ ሌላው በጥጋብ ሊኖር የሚችልበት ምክንያት የለምና ሃገሪቱ ያልታሰበ ቀውስ ውስጥ ልትገባ እንደምትቿል" ግምቱአን ገልጻለች።(ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በንግዱ ማህበረሰብ ላይ የጣለውን ግብር ለመሰረዝ መገደዱ ታወቀ፣ ድርጊቱ የአገዛዙን የዘፈቀደ አሰራር የሚያሳይ ነው ተባለ

ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በንግዱ ማህበረሰብ ላይ ጥሎት የነበረው ከፍተኛ የሆነ ግብር በበርካታ የህብረተሰቡ ክፍሎች ከፍተኛ ተቃውሞ ገጥሞት እንደቆየ የሚታወቀ ሲሆን፣ በተለያዩ አጀንዳዎች ተወጣጥሮ የሚገኘው አገዛዝ የዘፈቀደ ውሳኔውን እንደገና እንዲቀለብስ መገደዱን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ።

እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በቅርቡ ብሄራዊ ባንክ፤ ንግዱ ማህበረሰብና፤ የወያኔ ኢህአዴግ ባለስልጣናት ባደረጉት ስብሰባ ነጋዴዎች የአገዛዙ የግብር አጣጣል ስርአት በህይወታቸው ላይ ችግር እንደፈጠረባቸው ገልጸዋ። ይሁን እንጂ የዘረኛው አገዛዝ ሆድ አደር ካድሬ ሬዲዋን ሃሰን ነጋዴው ግብር የመክፈል ፍላጎት የለውም፣ አሁን በግብር አሰባሰብ ላይ የሚነሱት ቅሬታዎች ነጋዴዎች (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ትናንሽ ነውጦች ታላቁን ማዕበል ያስነሳሉ!!!

የሰደድ እሳትም ሆነ የውቅያኖስ ማዕበል በቀላሉ አይነሳም፤ ከተነሳ ደግሞ በቀላሉ አይቆምም። ህዝብ ተባብሮ በተነሳ ጊዜም ደን ውስጥ እንደተነሳ ሰደድ እሳት ወይም እንደ ውቅያኖስ ማዕበል ነው፤ ከባድ ጉልበትና ኃይል አለው። በመንገዱ ላይ ያሉትን ሁሉ አቃጥሎም ሆነ ደረማምሶ ማለፍ ይችላል። ዛሬ ሊቢያ ውስጥ እየሆነ ያለውም ይህንን የሰደድ እሳት ወይም የውቅያኖስ ማዕበል የመሰለን ህዝባዊ ንቅናቄ ነው።

ኮሎኔል ጋዳፊ ለተራዘመ ጦርነት ራሱን ሲያዘጋጅ እንደነበረ የቆፈራቸው ዋሻዎች እና በየቦታው ያከማቻቸው የጦር መሣሪያዎች ዓይነትና ብዛት ማረጋገጫዎች ናቸው። ሆኖም ግን ህዝባዊው ማዕበሉ እነዚህም ደረማምሶ ማለፍ ችሏል። ተመሳሳይ ክስተቶችን በሶሪያና በየመንም እናይ ይሆናል።

አገራችን ኢትዮጵያም ይህ ህዝባዊ ማዕበል እንደሚጎበኛት ይጠበቃል። ህዝባዊ ማዕበሎች አንዴ ከተቀሰቀሱ በኋላ የሚቀላቀላቸው ብዙ ነው። ከውስጥም ከውጭም የማዕበሉ አካል ለመሆን የሚፈልገው ሰው ቁጥሩ ብዙ ነው። ትልቁ ችግር ያለው ማዕበሉን ማስነሳት ላይ ነው።

ሁሌም ህዝባዊ ማዕበል የሚቀሰቀሰው በጥቂት ሰዎች ነው። እነዚህ በታሪክ ውስጥ አሻራቸው በወፍራው ታትሞ እንዲቀር የታደሉ ጥቂቶች ከየትኛውም የማኅበረሰብ ክፍል ሊወጡ ይችላሉ። የቱኒዚያው መሃመድ ቦዛዚ በታሪክ ስማቸው በጀግንነት እንዲነሳ ከታደሉት ወጣቶች አንዱ ነው። ሆኖም ግን እሱ የጫረውን እሳት ያቀጣጠሉ ሌሎች የአገሩ ዜጎች ባይኖሩ ኖሮ መላውን ሰሜን አፍሪካን ነፃ ያወጣው አብዮትን በአሁኑ ጊዜ ለማየት ባልተቻለ ነበር።

የአረብ ፀደይ የሚል ስያሜ የተሰጠውና በህዝብ ቀጥተኛ መሪነትና ተሳትፎ የተካሄደው የነፃነትና የማኅበራዊ ፍትህ አብዮት መዳረሻው የሁሉንም ዜጎች ክብርና መብት ማስከበር ቢሆንም በግንባር ቀደምትነት በወጣቶች የተመራና የተቀነባበረ ነው። ይህ አብዮት ለወጣቱ የወደፊት ህይወት ደንታ በሌላቸው ያረጁና ያፈጁ አምባገነን አገዛዞችና መሪዎች ላይ የገነፈለ ቁጣ ነው። በየሃገሩ የሚታየው ግብግብ ወደፊት በሚወለድ አዲስ የዴሞክራሲና የተስፋ ሥርዓት እና ባረጀና አንድ እግሩን ከመቃብር ጉድጓድ ከዶለ አምባገነናዊ አገዛዝ ጋር በመሆኑ ወጣቱን በስፋትና በሁሉም ዘረፍ ማሳተፉ የግድ ነው።

ከሰሃራ በታች ባሉ አምባገነንት በደደረባቸው ሃገሮችም ተመሳሳይ አብዮት መፈንዳቱ አይቀርም። የአፍሪካው ፀደይ እንደ አረብ አቻው ሁሉ የወጣቱ አሻራ እንደሚያርፍበት አያጠራጥርም። መፃዒ እድሉን ለመወሰን፤ ጽልመቱን ለመግፈፍ፤ እልሁም፣ ቁርጥኛነቱም፣ እውቀቱም፣ ብልሃቱም በወጣቱ እጅ ውስጥ እንደሆነ በቱኒዚያ፣ በግብጽ፣ በሊብያና በሶሪያ እያየነው ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የኢትዮጵያ ወጣት ለዚህ ኃላፊነት ብቁ ነው ብሎ ያምናል። በመለስ ዜናዊ አገዛዝ የወጣቱን ያህል የተበደለ የኢትዮጵያ የኅብረተሰብ ክፍል ማግኘት ይከብዳል።

መለስና እኩይ ቡድኑ የኢትዮጵያን ሃብት ተከፋፍለው ስለጨረሱት ለወጣቱ የተረፈው እዳ ብቻ ሆኗል። ለም መሬታችን ለባዕዳን በመሸጡ የገጠሩ ወጣት የሚያርሰው ቁራሽ መሬት እያጣ መሰደድ ከጀመረ ውሎ አድሯል። ወጣት ገበሬዎች ደቡብ አፍሪካ ድረስ ለመሰደድ ከቀያቸው ነቅለው የተነሱት በመለስ የአገዛዝ ዘመን ብቻ ነው። በገጠርም በከተማም የሚገኙ ወጣት ሴቶች ወደ አረብ አገራት ለመሄድ በረሃ ማቋረጥ፤ ባህርን በታንኳ መሻገር የጀመሩት በዚሁ የግፍ አገዛዝ ዘመን ነው።

ዘመናዊ ትምህርት ያገኘው ወጣትም በተማረው ትምህርት አገሩንና ወገኑን የማገልገል ህልሙ ተጨናግፎ ስደት እጣ ፈንታው የሆነው በመለስ የአገዛዝ ዘመን ነው። ለከፍተኛ ትምህርት እድል በህዝብ የተጠሉት የወያኔ ድርጅቶች አባል መሆን በመመዘኛነት የቀረበው በመለስ አገዛዝ ነው።

ኢትዮጵያዊ ወጣት ክብሩንና ነፃነቱን ለገንዘብና ለተሻሉ የሥራና የትምህርት እድሎች ሲል አሳልፎ እንዲሰጥ ሲደለል ቆይቷል። በዚህም ምክንያት አንዳንዱ ወጣት በወያኔ ሎሌነት ተሰልፎ የማያምንበት እየሰበከና እያደረገ ከህሊናው ጋር እንዲጣላ ተደርጓል።

ከዚህ ሁሉ የከፋው ደግሞ ወጣቱን በዘር በማደራጀት እርስ በርሱ እንዲጣላ መደረጉ ነው። በየጊዜው በሚፈለፈሉ "የወጣቶች ፎረሞች" አማካይነት የወጣቱ ወኔ ተሰልቦ አድርባይነትን እንዲለማመድ ተደርጓል። የጎንደሩ ለባሌ፤ የሸዋው ለአሩሲ፤ የትግራዩ ለባህርዳር፤ የሃረሩ ለጅጅጋው ባዕድ እንዲሆን፤ በጥርጣሬም እንዲጠባበቅ፤ በሰበብ አስባቡም እንዲቆራቆስ ተደርጓል።

ይህ ሁሉ ግን እየተቀየረ ነው። ወጣቱ "እኔ ምን አቅም አለኝ" የሚልበት ወቅት አልፏል። የወያኔ የአባልነት ደብተራቸውን የቀደዱ፤ "በፓርቲ ስብሰባ ላይ አንገኝም" ብለው መልዕክት የላኩ፤ የወያኔን "ድጎማ" አንቀበልም ያሉ፤ "ከዚህ በላይ ምን ይመጣብናል" በሚል ድፍረት የልባቸውን የተናገሩ ጀግኖች ብቅ ብቅ ማለት ጀምረዋል። እነዚህ ተናጠል የሚመስሉ እርምጃዎች እየተጠራቀሙ ህዝባዊውን ማዕበል ያስነሱታል።

ከእንግዲህ በኢትዮጵያ ውስጥ ለውጥ እንዲመጣ የሚፈልግ ዜጋ ሁሉ "የኔ ተሳትፎ ኢምንት ነው" ሳይል በተቻለው ሁሉ ትግሉን የሚያግዝበት ወቅት ላይ ደርሰናል ብሎ ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ያምናል።

የእያንዳንዳችንን ትናንሽ ተሳትፎዎችንም እያቀናጀን በማጎልበት ወደህዝባዊ ማዕበልነት ማድረስ የሁላችንም ሥራ ነው። ትናንሽ ነውጦች ሲጠራቀሙ ታላቁን ማዕበል ያስነሳሉ ብሎ ግንቦት 7 በጽኑ ያምናል።

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!!**

## ዊኪ ሊክስ ባለፈው ሳምንት ይፋ ባደረገው ምስጥራዊ ማስረጃ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ስለ ረቂቅ ህጉ ለአሜሪካው አምባሳደር ያማማቶ መግለጫ መስጠቱ የተገለጸው ብርሃኑ አዴሎ፤ የጸረሽብርተኝነት ህጉ አገዛዙን የሚቃወሙትን የፖለቲካ ተቃዋሚዎችን ለመከሰስ በተግባር ላይ የሚውል ሳይሆን በህዝብ ንብረትና ህይወት ላይ የሽብር ጥቃት ለመፈጸም የሚንቀሳቀሱትን ሽብርተኞች ለመከላከል ነው ብሎአል። መንግሥትን በሃይል ከሥልጣን ለማውረድም ሆነ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ለመግደል የሚደረግ ማንኛውም አይነት በማስረጃ የተደገፈ ወንጀል በመደበኛው የወንጀል ህግ ያስጠይቅ እንደሆን እንጂ በአዲሱ የሽብርተኝነት አዋጅ አያስከሥስም ያለው ብርሃኑ አዴሎ በምርጫ 97 የአዲስ አበባ ተመራጭ ከንቲባ የነበሩት የዶ|ር ብርሃኑ ነጋን ሥም ጠቅሶ የርሳቸው ህዝብን በመንግሥት ላይ ለአመጽ ማነሳሳትም ሆነ መንግሥትን በሃይል ለመለወጥ የሚያደረጉት ሙከራ በጸረ ሽብርተኝነት አዋጁ ሥር የሚፈረጅ አይደለም ማለቱም ተመዝግቦአል።

የጸረ ሽብርተኝነት ረቂቅ አዋጁ በፓርላማ ተብዬው የወያኔ ሸንጎ ቀርቦ ከመጽደቁ 4 ቀናት በፊት ለምን ለአሜሪካ ኤምባሲ ማቅረብ እንዳስፈለገ በሪፖርቱ ውስጥ የተገለጸ ነገር ባይኖርም ተቀማጭነታቸው በአዲስ አበባ የሆኑ አንዳንድ የምዕራባዊያን አገሮች ተወካዮችና የሰብ አዊ መብት ተሟጋቾች ረቂቁ ህጉን በግልጽ ቋንቋ ተቃውመውት ስለነበር የተነሳውን ተቃውሞ ለማመከን የአሜርካንን ድጋፍ ለማግኘት አስፈልጎአቸው እንደሆነ ግልጽ አድርጎታል።

የወያኔው ጀሌ ብርሃኑ አዴሎ የጸረ ሽብርተኝነት አዋጁ የፖለቲካ ተቃውሞን ለመደፍጠጥ አይደለም ይበል እንጂ ዲሞክራሲን በአገሪቱ ለማስፈን ይቻል ዘንድ የመንግሥት ለውጥ ያስፈልጋል ብሎ በመንቀሳቀስ ላይ የሚገኘው ድርጅታችን ግንቦት 7ን ጨምሮ ኦነግንና ኦብነግን በሽብርተንነት መፈረጃቸው የአደባባይ ምስጥር ነው። አምባገነኖች መውደቂያቸው ሲቃረብ የሚቃወማቸውን ሁሉ በበሽብርተኝነት እንደሚከሱ ከቱኒዚያው ቤን አሊ ከግብጹ ሆሴን ሞባረክና ከሊቢያው ጋዳፊ የተመለከትነው ስለሆነ ህዝባችን የመለስ ዜናዊን ዘረኛ አምባገነን አገዛዝ ከትክሻው ላይ አሽቀንጥሮ ለመጣል የሚያደረገውን ትግል እስከመጨረሻው እንደሚገፋበት የግንቦት 7 እምነት ነዉ።

## ዘረኛውና አምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ በንጹሃን ዜጎች ላይ

. . . (ከገጽ 1 የዞረ)

እንደ ኢሳት ዘገባ ከውስጥ በህዝባዊ ብሶት ፤ከውጪ በዓረብ አገራት በተከሰተው አብዮት ከፍ ያለ ውጥረት ውስጥ የገባው ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ የኦሮሞ ነፃነት ግንባርን፣ የኦጋዴ ብሄራዊ ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄንና ግንቦት ሰባትን "በሽብርተኝነት" በመፈረጅ -በህሳባቸው ለአገዛዙ ስጋት መስለው የሚታዩ ዜጎችን ሀሉ ከሶስቱ ድርጅቶች ከአንዱ ጋር በማገናኘት ማሰርን እንደ አቅጣጫ መያዙን፤ ውስጥ አዋቂዎች ገልጸዋል ብሉአል።

የወቅቱ የኦፌዲንና የመድረክ ሊቀመንበር ዶክተር ሞጋ ፊሪሳ ፤ የዘረኛው አገዛዝ በታሰሩት የተቃዋሚ ፓርቲ መሪዎች ላይ የሚያሰማውን ክስ ያጣጣሉት ሲሆን፤ ሁለቱም የታሰሩት ከፓርቲዎቻቸው ባገኙት ውክልና መሰረት ከውጪ አካላት ጋር ግንኙነቶችን ያደርጉ ነበር ማለታቸውን ጠቅሱአል። በመቀጠልም በነዚህ ግንኙነታቸው በተለይ በደቡብ ኢትዮጵያ በርቀት በሚገኙ አካባቢዎች ስለተከሰቱ ድርቆች ተከታትለው የሚሰጧቸው መረጃዎች፤ በተደጋጋሚ ዘረኛው አገዛዝ ሲለው ከነበረው ጋር ይጋጩ እንደነበር ዶክተር ሞጋ ማስታወሳቸው ን ኢሳት ገልጹአል።

በተለይ አቶ በቀለ ገርባ- በቅርቡ "የኢትዮጵያ መንግስት በቢሊዮን የሚቆጠር የእርዳታ ገንዘብን የፖለቲካ መጠቀሚያ አድርጎታል"በማለት ቢቢሲ ይፋ ላደረገው ዘገባ :-"መረጃ ሰጥታችሁዋል" ተብለው ስለታሰሩት ሰዎች በተደጋጋሚ ሲናገሩ መቆየታቸውን ዶክተር ሞጋ የገለጹ ሲሆን በቢቢሲ የምርምራ ዘገባ ፤"ባለፈው ምርጫ ድምፃችሁን ለኢህአዴግ አልሰጣችሁም" የተባሉ ዜጎች እርዳታ ተከልክለው፤ በረሀብ አንጀታቸው ብሶታቸውን ሲያሰሙ መታዬታቸው፤ የብዙዎችን ስሜት መንካቱና የዓለማቀፉ ማህበረሰብ መነጋገሪያ እየሆነ መምጣቱ ይታወቃል።

በርካታ ኢትዮጵያዊያን በየቀኑ በርሃብ አለንጋ እንደቅጠል እየረገፉ ባሉበት ሁኔታ "በኢትዮጵያ ድርቅ እንጂ ርሀብ የለም" የሚለው የአረመኔው መለስ አገዛዝ፤ በደቡብ ኢትዮጵያ እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ሰዎች፤ 200 ሺህ ብቻ እንደሆኑ በተደጋጋሚ ቢናገርም፤ የአሜሪካ የእርዳታ ባለስልጣናት ሳይቀሩ ወደ ስፍራው በመንቀሳቀስ ባደረጉት ቅኝት የተረጅዎች ቁጥር ከ 700 ሺህ እንደሚበልጥ ይፋ ማድረጋቸው አይዘነጋም።

ከዚሁ ጋር በተያያዘ የወያኔ ዘረኛ አገዛዝ በቢቢሲ የምርመራ ዘገባ ላይ አስተያየታቸው የተካተተውን ፕሮፌሰር በየነ ጴጥሮስን፣ ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያምንና ዶክተር መረራ ጉዲናን በአገር ክህደት በመወንጀል በሚቆጣጠራቸው መገናኛ ብዙሀን ሳምንታት የዘለቀ ዘመቻ ከፍቶባቸው መቆየቱ በስፋት መዘገቡ ይታወሳል።

## የግንቦት7 አላማ ምንነት፤ ለምንና እንዴት በሚል ርዕስ ከታተመው የግንቦት7 መጽሃፍ የተወሰደ ( ክፍል 3 ካለፈው ሳምንት የቀጠለ )

ሳይንቲስት ነኝ፤ ኢኮኖሚስት ነኝ፤ ሃኪም ነኝ፤ ቄስ ነኝ፤ አርቲስት ነኝ፤ ነጋዴ ነኝ" የሚለው ዜጋ የነጻነቱን ጉዳይ የፖለቲካ ሰዎች ሥራ አድርጎ ሲተወው የሚሰራውን ያውቃል፡፡ እራሱን ለገዛ ነጻነቱና ስብእናው ከመታገል እያሸሸ እንደሆነ ያውቃል፡፡ ሆድ ሲውቅ ዶሮ ማታ ነውና ለራሱ እየቀጠፈ እንደሆነ ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም ጋዜጠኛው እውነቱን አትጻፍ ሲባል፤ ነጋዴው «ጫማ ስመህ ጉቦ ሰጥተህ እቃህ ከጉምሩክ ይለቀቃል» ሲባል፤ ፕሮፌሰሩ «ተማሪዎችህን እኛ ከፈቀድነው ውጭ ጥያቄ ማንሳት ውይይት እንዲያደርጉ ማድረግ አትችልም» ሲባል፤ ተማሪው «ለከፍተኛ ትምህርትና ሥራ ለመቀጠር የመለስ ዜናዊ ጀሌ የግድ መሆን አለብህ» ሲባል፣ አንድ ዜጋ በዘሩ እየተለየ ጥቃት ሲደርስበት፣ በእምነቱ የተነሳ ሲዋረድ፤ እየተገፈፈ ያለው ከስብእናው ጋር የመጣውን ነጻነቱን ነው፡፡ ከነጻነቱ ጋር የመጣውን ስብእናውን ነው፡፡ ይህን ዓይነቱን የነጻነት ማስከበር ሥራ ለፖለቲከኞች መተው የሚቻለው ራስን በከፍተኛ ማጭበርበር በመሙላት ብቻ ነው፡፡ በሃገር ውስጥም ሆነ ከሃገር ውጭ በእንዲህ አይነቱ የራስ ማጭበርበር የተሞላ የውሸት ህይወት የምንኖረው ብዙዎች ነን፡፡

ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ሃገራቸውን ለቀው በሚሊዮኖች የሚሰደዱት በፖለቲካ ሆነ በኢኮኖሚ ምክንያት በሃገራቸው መኖር ስላልቻሉ እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ በየጊዜው የመጡ አምባገነን መሪዎች እንደቆሻሻ እየጠረጉ አያት ቅድመ-አያቶቻችን የደም መባ ገብረው በነጻነቷ ታፍራ እንድተቆይ ካደረጓት ሃገር እንዳላባረሩን፣ ብዙዎቻችን ስደትን በምርጫችን የገባንበት ጉዳይ አድርገን የምናይበት ህሊና በፍጥነት እንገነባለን፡፡ ለአሳፋሪ የስደት ህይወት ከተዳረግን ጥቂት አመታት በኋላ የምናገኘውን የሌላ ሃገር ዜግነት ለነጻነታችን መቆም ባለመቻላችን በተነጥቅነው ዜግነት ምትክ ተክተን፣ ለስደት በበቃንበት ሃገር የቆየነው ዘመን ገና አንድ ትውልድ ሳይሞላው፣ «እኔ አሜሪካዊው፣ እኔ እንግሊዙ እኔ ጀርመኑ» ስንል ምንም እፍረት አይሰማንም፡፡ ይህ እፍረት ማጣት ሌላው ራስን የማጭበርበር ውጤት ነው፡፡

ቀደም ብለን በእዚህ ጽሁፍ መጀመሪያ እንደጠቀስነው እኛ ኢትዮጵያውያን ከየትኛውም ነጻነት በላይ ትልቅ ቦታ ሰጥተነው የኖርነው የሃገራችንን ነጻነት ነው፡፡ ቀደምቶቻችን ለሺህ አመታት አይችሉት ፈተናዎችን ችለው፣ አይከፍሉት መስዋእትነት ከፍለው እንዳቆዩልን የሃገር ነጻነትና ከውጭ ወራሪዎች ነጻ ሆኖ የመገኘት ነጻነት በላይ የሚያኮራን ቅርስ የለንም፡፡ እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ሌላም ቅርስ የለንም፡፡ ይህንን ሃገር ለዝንተ አለም ቀደምቶቻችን እየወደቁና እየተነሱ ልጆቻቸውን በየሜዳው እየበተኑ በየዱሩና በየጫካው እየወደቁ ለእኛ ለልጆቻቸው እንዳስረከቡ እናውቃለን፡፡ እኛም ብንሆን ይህንን ሃገር ሲቻል ከቀደምቶቻችን በተሻለ ካልሆነም እንደነበረ ለመጪው ትውልድ ከማስረከብ የላቀ የትውልድና የታሪክ አደራ እንደሌለብን እናውቃለን፡፡

ስለሃገራችን ስናስብ የማናመልጠው ሃቅ ቢኖር እኛ መርጠን የተወለድንበት ቦታ አለመሆኑን ነው፡፡ ወላጆቻችንን አልመረጥንም፣ የተወለድንበትን ቤተሰብ፣ አልመረጥንም፣ ቋንቋችንን አልመረጥንም፣ የቆዳችንን ቀለም፣ የአካላችንን ቅርጽ አልመረጥንም፡፡ ለብዙዎቻችን ከሃገራችን ጋር ያለን ቁርኝት የጠበቀ የሆነው ለሃገራችንና ወገናችንም ለምንለው ኢትዮጵያዊ የተለየ ስሜት እንድንይዝ የሚያደርግን ይህ ነው፡፡

ቀደም ብለን የጠቀስነው የፈረንጆቹን ፓስፖርት የወረሰውና እራሱን የፈረንጆቹ ዜጋ አድርጎ የወሰደው ወገናችን ነገ እነዚህ ፈረንጆች ኢትዮጵያን ቢወሩ፣ በሌሎች ሃገሮች ላይ የሚጠቀሟቸውን አስከፊ መሳሪያዎች በደሃ ኢትዮጵያውያን ላይ ቢያዘንቡ ምን ስሜት እንደሚሰማው ለማወቅ ጠንቋይ መቀለብ አይኖርብንም፡፡ ሌላው ቀርቶ ኢትዮጵያውያን ወንድና ሴት አትሌቶች ከሌሎች ሃገር ዜጎች ጋር ሩጫ ሲፎካከሩ በቴሌቪዥን ስናይ የሚሰማንን እናውቃለን፡፡ የዜግነት ፓስፖርት የሰጡን ፈረንጆች እንዲያሸንፉዋቸው አንመኝም፡፡ እኛ ብቻ አይደለንም። ገና ያልተረገዙ ልጆቻችን ከፎቴው ጠርዝ ላይ ተቀምጠው ልባቸው እየመታ የአትሌቶቻችንን አሸናፊነት ሲመኙ ማለም አያዳግተንም፡፡

ነገር ግን ከላይ የጠቀስነው የፈረንጅ ዜግነት በማግኘቱ ፈረንጅ ነኝ የሚለውም ሆነ፤ ሌላውም በፈረንጆች ሃገር ተምሮ በአንድ ትልቅ ዩኒቨርስቲ አንቱ የተባለ ፕሮፌሰር የሆነው፣ ወይም ነግዶ ብዙ ሃብት ያካበተና በትልቅ ቤት የሚኖረውና ውድ መኪና የሚያሽከርክረው ስደተኛ የሚሰማው የክንዋኔ ኩራት ራስን በመሸንገል ብቻ የሚገኝ ነው፡፡ ከማንነቱና ከምንነቱ ጋር በብዙ ክሮች የተተበተበበትን የቋንቋው፣ የመልኩና የታሪኩ መሰረት ከሆነችው በብዙ ፈተና ቀደምቶቹ ካስረከቡት ሃገር ተገፍቶ ወጥቶ፣ ቀደምቶቹ ለእራሱ ያስረከቡትን ሃገር እሱም ለልጆቹ ማስረከብ በማይችልበት ሁኔታ ተቀምጦ በፈረንጅ ሃገር ተገኘ የሚለው የህይወት ድል በየትኛውም የክንዋኔ መለኪያ ቢላክ ባዶ ድል መሆኑን ልቡ ያውቀዋል፡፡

«ስለሃገርና ስለወገን ጉዳይ አታንሱልኝ ብሎ» ቤቱን ግን ኢትዮጵያን በሚያስታውስ ቅርጻ ቅርጽ ሞልቶ፣ ጥሬ ስጋና ክትፎ እየበላ፣ በሺ የሚቆጠሩ ኪሎ ሜትሮች አስጉዞ ባስመጣቸው ታቦቶቹ ስም በሰራው ቤተስኪያን በየሳምንቱ ጸሎት የሚደርሰው ፣ በየመስጊዱ ዱአ የሚያደርገው፣ ሽሚዝና ከረባቱ ሳይቀር ወጥ ወጥ እየሸተተ ሥራ የሚገባው ኢትዮጵያዊ ማንን ነው የሚያታልለው? ኢትዮጵያውያን በየደረሱበት ባህላቸውን፣ ቋንቋቸውንና ከሃገራቸው ጋር ያላቸውን ትስስር በአንቀልባ አዝለው እንደሚጓዙ እያወቅን የኢትዮጵያ ጉዳይ አይመለከተንም ሲሉ ብንሰማቸው ልንገረም አይገባም፡፡ የኢትዮጵያዊነት ስሜት በራሱ ከነጻነት ስሜት ጋር የተሳሰረ እንደሆነ ስለምናወቅ ሽሽታችን ከሃገራችን ሳይሆን ከነጻነታችን ነው፡፡ የኢትዮጵያ ጉዳይ አይመለከተኝም የሚለው አባባል ለኢትዮጵያ ያለን ጥላቻ ሳይሆን ለገዛ ነጻነታችን ያለንን ፍራቻ የሚረጋግጥ ነውና፡፡

ከእዚህ በላይ የተባለው ሁሉ የሚያሳየው አንድ ነገር ብቻ ነው፡፡ ነጻነታችንን በመሸሽ የምንመራው ህይወት በሃሰትና በራስ ሽንገላ የተሞላ ህይወት መሆኑን ነው። ይህ የሃሰት ህይወት ከትላልቅ የሃገር ጉዳይ አንስቶ እስከ ተራ ህይወታችን ድረስ ይዘልቃል፡፡ የሃሰት ህይወት ደግሞ በማንኛውም መመዘኛ ኢሞራላዊ የሆነ እንደሰው ነጻ ሆኖ ከተፈጠረ ሃያል ፍጡር የማይጠበቅ ነው፡፡

### ነጻነትና ባህል

በሃገራችን ውስጥ ከእዚህ በላይ የጠቀስነውን የነጻነት ምንነትና ትርጉም ለማሰላሰል የቻልንበት ማህበራዊና ምሁራዊ ሁኔታ አናገኝም፡፡ የተናጠል ጥረቶች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በሃገራችን ለዘመናት የኖረው አፋኝ የፖለቲካና ባህላዊ ሁኔታ ይህ በግለሰብ ደረጃ ሊሰማን ስለሚገባው ሰብአዊ ነጻነት እድል የማይሰጥ በመሆኑ ህብረተሰባችን ለእንዲህ አይነቱ የነጻነት አመለካከት ባእድ ሆኖ ኖሯል፡፡ በእምነት ደረጃ ሰው አስቀድሞ እጣውና ውሉ የተሰመረ እንደሆነ እየተነገረን፣ በግል ጥረት ልንደርስበት የምንችለውን ክንዋኔ አንኳሰን እንድናይ ስንሰበክ ነው የኖርነው፡፡

በራስህ ውሳኔ ኑር ተብሎ ከገነት/ጀኔት ሰው ተገፍትሮ መውጣቱን የሚያስተምሩን ሃይማኖቶቻችን ሳይቀሩ፣ ፈጣሪ ሰው በውሳኔው እራሱን እየፈጠረ እንዲኖር የሰጠውን ብይን የሚቃረን ትምህርት ሲያስተምሩን ኑረዋል፡፡ በሃገራችን ሆነ በውጭ ሃገር ከምናየው ተጨባጭ ማስረጃ ውጭ እጣችን አስቀድሞ የተደነገገ ምንም ብናደርገው የማንቀይረው ተደርገን ስንሰበክ ኖረናል፡፡ መሳፍንቱ መሳፍንት እንደሆኑ ከነድሎታቸው፣ ገበሬውም ገበሬ እንደሆነ ከነዝተቱ ለዝንተአለም እንደሚኖሩ፣ ደህነትንና መብት ረገጣን በሰውነታችን ልናምጽባቸውና ልናሸንፋቸው የምንችል ጉዳዮች እንዳልሆኑ ሲነገረን ቆይተናል፡፡

የፖለቲካ ሥርዓቱም ሰውን በእቃና በባሪያ ደረጃ ከማየት ውጭ ስለራሳቸውም ይሁን ስለሌው ነጻነት ቀደም ብለን የጠቀስነውን ግንዛቤ ባልያዙ ድውያን እጅ በተከታታይ በመውደቁ ከመሪዎች ወደ ህዝብ ሊወርድ የቻለ የነጻነት ቡራኬ አልታየም፡፡ ከታች ወደ ላይ ነጻነትን ለማስከበር የተደረጉ አመጻዎች ለዘመናት በሽንፈት የተጠቃለሉበት ወይም አሸናፊው ነጻ አውጭ ነኝ ባይ ወደ ሌላ ባራያ ገዥነት የተቀየረበት ሁኔታ በመከሰቱ፤ በህብረተሰባችን ውስጥ ምንም ነገር አይቀየርም የሚል አመለካከት እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ ተረትና ምሳሌዎቻችን በሙሉ፣ እነ ጎመን በጤናን፣ አጉል መፈራገጥ ለመመላለጥ የመሳሰሉት፣ ነገሮችን አትነካካ የምትቀይረው ነገር የለም የሚለውን አመለካከት የሚያጠናክሩ ናቸው፡፡

ህብረተሰባችን በአዛዝና በታዛዥ በጌታና በሎሌ ግንኙነት ተተብትቦ ለረጅም ዘመን የኖረ በመሆኑ ይህንኑ የእዝ ሰንሰለት የሚያንጸባርቁ አመለካከቶች ናቸው በሃገራችን ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የቆዩት፡፡ በቃን ብለው የተነሱ ዜጎች በየጊዜው የገጠማቸውን ስቃይና መከራ ለዘመናት ሲያስታውስ የሚኖር ትውልድ አበሳው ሲበዛበት፣ ማመጽን ሳይሆን ምንም ማድረግ አይቻልም ወደሚል የራስ ሃላፊነትና የየራሱን ሰብአዊ የድርጊት ነጻነት መካድ ውስጥ ይገባል፡፡ ማለቂያ የሌላቸውን ምክንያቶች በመደርደር እንደ አንድ ሃገር ዜጋ ብቻ ሳይሆን እንደሰው ልንቀበለው የማይገባንን እጅግ አሳፋሪ ሃገራዊና ማህበራዊ ሁኔታ ተቀብለነው መኖር የምንችለው ለእዚህ ብቻ ነው፡፡

ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚታየውን የሰብእና መራከስ ውርደትና አሰቃቂ ድህነት እያየን እንዳላየን ማለፍ የምንችለው ቀደም ብለን እራሳችንን ከሰውነት አውርደን በእቃነት ለማስቀመጥ በመቻላችን ብቻ ነው፡፡ ራሳችንን በእቃነት ለማስቀመጥ ፍላጎቱ እስካለን ድረስ ደግሞ በእቃነት ሊያስተናግዱን ዝግጁ የሆኑ ሌሎች ሰዎች ሁሌም እንዳሉ መረዳት ይኖርብናል፡፡ መብታችንን ከሚገፉት በላይ መብታችን በተለያዩ ምክንያቶች እንዲገፈፍ የፈቀድነው ግለሰቦች ነን በቅድሚያ ተወንጃይና ተወጋዥ መሆን የሚገባን፡፡ ከግል ሰብብ አንስተን በባህልና በማህበረሰብ ከወረስናቸው ዝንባሌዎች ጭምር አንዳቸውም ለነጻነታችን ላለመታገል ምክንያት መሆን እንደማይችሉ ግን እናውቃለን፡፡ የሚቀረን ይህንን እውቀት ከምር ወስደን በተግባር መተርጎም ብቻ ነው፡፡

### ዜግነትና ነጻነት

የዜግነት ነጻነት ለሁላችንም በእኩልነት ከተላበስነው ሰብአዊ ነጻነት የሚመነጭ ነው። የዜግነት ነጻነት የምንላቸው የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀትና ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስና ሌሎች መብቶች በሙሉ የሰብአዊ ነጻነታችን ቅርንጫፎች ናቸው፡፡ እነዚህን መብቶች ማንም እንዲገፋቸው ልንፈቅድለት የማንችለው ይህ ገፈፋ በቀጥታ ሰው አይደላችሁም የሚል መልእክት ስለሚያስተላልፍ ነው፡፡ ለእነዚህ መብቶች የሚደረግ ትግል ሰብአዊ ፍጡርነትን ለመከላከል የሚደረግ ትግል ነው፡፡

የዜጎች ነጻነት ግን ከዚህም ሰብአዊ ማንንት ጋር ከተሳሰረ ጉዳይ በላይ ሌላም ተጨማሪ ትርጉም አለው፡፡ ሰው የሚኖረው በማህበረሰብ ውስጥ ነው፡፡ ማህበረሰብ ማለት ሌላ ትርጉም የለውም፡፡ የሰው ማህበር ማለት ነው፡፡ በእዚህ ማህበረሰብ ሰዎች ተሰባስበው የሚያደርጉት ማህበራዊ እንቅስቃሴ ሁሉንም በእኩልነት በሚያዩ በጋራ ስምምነት የተደረሰባቸው ውሎችና ህጎች አማካይነት ነው፡፡ በእነዚህ የእኩልነት ውሎች ስር እያንዳንዱ ዜጋ በነጻነት የሚያደርገው እንቅስቃሴ በተከበረባቸው ቦታዎች በመሉ የሰው ልጅ የተረጋጋና የበለጸገ፣ ለሰው ልጆች ስቃይ የሚጨነቅ ማህበረሰብ መፍጠር የተቻለበት ሁኔታ እንዳለ እናውቃለን፡፡

ዜጎችን እኛ እናውቅልሃለን በሚል የጥቂቶች ፈላጭ ቆራጭነት ስር አስገብተው የሚገዙ ስርአቶች በሞራል ኪሳራ የተሞሉ ብቻ አይደሉም፡፡ በሁሉም መስኩ መከራ አምራቾች ጭምር ናቸው፡፡ ይህ ሃቅ እኛ የግንቦት7 አባላት ለዜጎች ነጻነት እንድንቆም የሚያደርገን ተጨማሪ ምክንያት ነው፡፡ ነጻነት በማይከበርብት ሁኔታ የሚራከሰው ሰብአዊነት ብቻ ሳይሆን ማህበረሳባዊነትም ጭምር ነው፡፡ በሃገራችን የዜጎች የፖለቲካ ነጻነት እንዲከበር የግንቦት 7 ንቅናቄ ዋነኛው አጀንዳው አደርጎ የሚታገለውም ለእዚህ ነው፡፡ የፖለቲካ ነጻነት ስንል ምን ማለታችን እንደሆነ የሚገልጸው የመጨረሻው ክፍል ከእዚህ የሚቀጥለው ነው፡፡

(ክፍል 4 ሳምንት ይቀጥላል)

## ህዝባዊ አመጽ እንዳይነሳበት በፍርሃት የተጠመደው የወያኔ አገዛዝ በሰሜን ጎንደር የነዋሪዎችን ቤት ያለአግባብ መፈተሽ ጀመረ

ህዝብን በመሳሪያ ሃይል አንቀጥቅጦ እስከወዲያኛው የመግዛት ዕቅዱ እንደማይሳካ እየተረዳ የመጣው የዘረኛው መለስ ዜናዊ አገዛዝ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሰሜን ጎንደር የህዝቡን የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ በጥብቅ ከመከታተል አልፎ ባልተጠበቀ ሰዓት በሠላማዊ ዜጎች ቤት ዘው ብሎ በመግባት የመሳሪያ ፍትሻ ማካሄድ እንደጀመረ ዘጋቢያችን ከስፍራው በላከልን ዜና ገለጸ።

በአሁኑ ሰዓት በመላው አገሪቱ እየተባባሰ በመጣው የኑሮ ውድነት ምክንያት ህዝብ በአገዛዙ ላይ ያለው ጥላቻ ሊደበቅ ከሚችለው በላይ በመሆኑ የተደናገጡት የአገዛዙ ሹመኞች በቀጭን ትዕዛዝ የሚያሽከረክሩዋቸው ፍርድ ቤቶችን በክልሉ ለተጀመረው የነዋሪዎች ቤት ፍተሻ ተባባሪ በማድረግ የተፈላጊ ሰው ሥም ያልተጻፈበት ባዶ የቤት ፍተሻ ማዘዣ ለፖሊስ እንዲሰጡ እንዳደረጉዋቸው ታውቆአል። በዚህም ምክንያት ፖሊሶች ባሰኛቸው ቀንና ሰዓት የፈለጉትን ሰው ሥም በያዙት የፍርድ ቤት ማዘዣ ላይ እየሞሉ ያለምንም በቂ ምክንያት የግለሰቦችን ቤት እየፈተሹ ናቸው ተብሎአል።

ምክንያቱ በግልጽ ባልተነገራቸው ወንጀል ጥርጣሬ ቤታቸው የተፈተሸባቸው ሰዎች ለዘጋቢያችን እንደገለጹት፤ ቁጥራቸው እስከ 3 የሚደርስ ፈታሾች በያንዳንዳቸው ቤት በድንገት ዘው ብለው በመግባት መሳሪያና ሌላም ለመንግሥት ደህንነት የሚያሰጋ ነገር ቤታቸው ውስጥ አለመኖሩን ለማረጋገጥ እንደሚፈልጉ በመናገር በእጃቸው የያዙትን የፍርድቤት ማዘዣ ካሳዩ ቦኋላ ፍተሻ አካሂደው ወደመጡበት ይመለሳሉ።

እንደዘጋቢያችን መረጃ የፍተሻው ኢላማ የሆኑት ሰዎች እንደተቀረው የአገሪቱ ክልሎች በዞኑ እየተባባሰ በመጣው የኑሮ ውደነቱ በአገዛዙ ላይ አመጽ ሊያስነሱ ይችላሉ ተብሎ የሚፈሩና የሚጠረጠሩ በአብዛኛው በወጣትነትና በጎልማሳነት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን እንደሆነም ታውቆአል።

ይህ በዚህ እንዳለ በደቡብ ክልል በአገረ ማርያም ወረዳ የሚገኙ ለፋሽስቱ የወያኔ ፓርቲ ፍቅር እንደሌላቸው የሚጠረጠሩ ዜጎች ገዢውን ፓርቲ አትደግፉም በሚል ሰበብ የንግድ ፈቃድ ለማውጣት እንደተከለከሉ ተዘገበ።

በከተማው ነዋሪ የሆኑና በንግድ ሥራ የሚተዳደሩ ሀጂ ኡመር ሀሰን የተባሉ ነጋዴ ሰሞኑን የስኳር ንግድ ፈቃድ ማውጣት እንደሚቻል በወጣው ማስታወቂያ መሠረት ፈቃዱን ለማግኘት ወደ ፈቃድ ሰጪው መሥርያቤት ቢሄዱም" እርስዎ ተቃዋሚዎችን ይደግፋሉ" ተብለው መከልከላቸውን ኢሳት ዘጋቦአል። ከሀጂ ኡመር በተጨማሪ ሌሎች በርካታ ሰዎች የተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ስም እየተጠራላቸው፤ የዚህ ፓርቲ ደጋፊ ስለሆንክ ፈቃድ አንሰጥም ተብሎ እንደተነገራቸው ለማወቅ ተችሎአል።

በፍትህ ሚንስቴር የሚሠሩ ዳኞች የወያኔ አባል ካልሆናችሁ በቀር የጥብቅና ፍቃድ አይሰጣችሁም መባላቸውን መዘገባችን ሲታወቅ ሰሞኑን ደግሞ የኢህአዴግ አባላት አንሆንም በማለታቸው ከስራ የተባረሩትን የመንግሥት ሠራተኞች ኢሳት እንዳነጋገረ ይታወሳል።

## የአለም የገንዘብ ተቋአም ኢትዮጵያን ያልታደለች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የዋጋ ግሽበቱን አስመልክቶ የወያኔዉ ባለሥልጣናት የተምታታና ወጥ ያልሆነ ምክንያት በማቅረብ ላይ እንዳሉም ታዉቁአል። ለዚህም የወያኔዉ ባለስልጣናት ልል የሆነ የገንዘብ ፖሊሲ (Loose Monetary Policy) እንደሚከተል ሲያምን፣ በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የዋጋ ግሽበቱ ዋነኛ ምክንያት ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የገባ የዋጋ ግሽበት ነው ብሎ እንደሚያምንና አይኤምኤፍም ይኼንን የክርክር ነጥብ ውድቅ እንዳዳረገው በሪፖርቱ ውስጥ እንደተገለጠ ም ጠቁሙአል፡፡ይልቁንም የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚያሳትመው ገንዘብ (Base Money) በዓመታዊ ንፅፅር 42 በመቶ መጨመሩን፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክም የሰጠው ብድር የ45 በመቶ ጭማሪ በማሳየቱ ለዋጋ ግሽበቱ ዋነኛ ምክንያቶች መሆናቸውን አይኤምኤፍ በሪፖርቱ ውስጥ አሳይቱአል።

አይ ኤም ኤፍ ለማክሮ ኢኮኖሚዉ አሉታዊ የሆኑ አሳሳቢ ጉዳዮች በማለት የተቸዉ የወያኔ አገዛዝ የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚን በተመለከተ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ያለጥናት የሚያወጣቸዉ የቁጥጥር መመርያዎች የዘርፉን እንቅስቃሴ እየገቱና እምነቱን እየጐዱ (Damaging Private Sector Confidence) መሆኑንም ነዉ። አገዛዙ በግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ላይ በተለይም በፋይናንሱ ዘርፍ በተሰማሩት ላይ የሚያደርሰዉን ጫና ለማሳየት ዋቢ ያድርገዉ እ.ኤ.አ ከሚያዚያ 2010 ወዲህ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የግል ንግድ ባንኮች ካበደሩት ብድር ውስጥ 27 በመቶ የሚሆነውን የብሔራዊ ባንክን ቢል (ቦንድ) እንዲገዙ በማስገደዱ፣ ይኼ መመርያ ከወጣ ወዲህ የግል ባንኮች በአምስት በመቶ ወለድ ከአስቀማጮች ካሰበሰቡት ገንዘብ ዉሳጥ 27 በመቶ የሚሆነውን በሦስት በመቶ ወለድ ለብሄራዊ ባነኩ እንዲያበድሩና ብሔራዊ ባንክም ከግል ባንኮቹ ያገኘውን ገንዘብ በወያኔ ቁጥጥር ስር ላሉት ለኢትዮጵያ ልማት ባንክና ለኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በመስጠት፣ የማበደር አቅማቸውን እንዲያጠናክሩና እንዲያተርፉ ማድረጉ ፍፁም ኢ/ ፍትሐዊ ና የፋይናንስ ተቋማትን ዕድገት የሚያቀጭጭ መሆኑን በሪፖርቱ ውስጥ ካካተታቸው ጉዳዮች አንዱና ዋነና ነው፡፡

የወያኔዉ አገዛዝ ኢኮኖሚው ዘንድሮ በ11 በመቶ ማደጉንና በቀጣይ ዓመታትም ይኼንኑ ዕድገት እንደሚያስቀጥል ቢጠቅስም፣ አይኤምኤፍ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ዕድገት ወደ6.5 በመቶ እንደሚወርድ ትንበያውን አስፍሯል፡፡

አይኤምኤፍ ቀደም ሲል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ከሚከተለው ልቅ የሆነ የገንዘብ ፖሊሲና ብር እያተመ ከማሰራጨት ተግባሩ እንዲታቀብ፣ የወለድ ምጣኔን እንዲያስተካክል፣ የኢኮኖሚ መዋቅር ማሻሻያዎችና የንግድና የውጭ ምንዛሪ ማሻሻያዎች እንዲደረጉ የወያኔን ገዢዎች መምከሩን፣ ቀደም ብለን መዘገባችን አይዘነጋም።

አይ ኤም ኤፍም በማጠቃለል ሁኔታዎች ከመሻሻል ይልቅ ተባብሰው የተገኙ መሆናቸውን በማስታወስ አለመታደል (Unfortunate) ነዉ ሲል ማስፈሩን ለማወቅ ተችሎአል፡፡

ሪፖርቱ ጠንካራ ቃላትን በመጠቀም የወያኔን ባለስልጣኖች ክፉኛ የተቸ በመሆኑ፣ ለአባል አገሮችና ለሕዝብ በኢንተርኔት እንዳይሰራጭ አገዛዙ ያገደ መሆኑን የገለጠዉ ሪፖርተር ይሁን እንጂ የአይኤምኤፍ የዳይሬክተሮች ቦርድ በሪፖርቱ ላይ አቋም ሳይዝ እንዳልቀረም የዓለም ባንክ ምንጮቹን ዋቢ አድርጎ ገልጸዋል፡፡ ከዚሁ ጋር በተያይዘም እንደአውሮፓዊያን አቆጣጠር ሜይ 31 ቀን 2011 አይ ኤም ኤፍ በተመሳሳይ ዘገባው አገዛዙ ያወጣው የአምስት አመት ትራንስፎርሜሽን እቅድ ሊሳካ የማይችልና ላም አለኝ በሰማይ በሰማይ አይነት እንደሆነ መግለጹን መዘገባችን ይታወሳል፡፡

## በኢትዮጵያ የኑሮ ውድነትና ስራ አጥነት ተባብሰዋል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በተመሳሳይ መልኩ በደቡብ ዩኒቨርሲቲ በግብርና ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪዉን የያዘና ስሙ እንዳይጠቀስ የጠየቀ ወጣት በሰጠው አስተያየት ከስራ አጥነቱ በተጨማሪ ባሁኑ ሰአት በሃገሪቱ ያለው የኑሮ ውድነት የሞት የሽረት ቁዋፍ ላይ እንድንቀመጥ ስላደረገን፣ አይናችን እያየ እየተራብን ከመሞታችን በፊት፣ ችግሮች ሊወገዱ ለሚችሉበትና አገዛዙን ከጫንቃችን ላይ አሽቀንጥረን ለመጣል በሚደረገው ትግል የግንባር ቀደምትነቱን ድርሻ እንይዛለን በማለት ተናግሩዋል።

ለተፈጠረው ችግር ተጠያቂው ማን ነው ትላላችሁ በማለት ዘጋቢያችን ላቀረበው ጥያቄ ሁለቱም ወጣት ተመራቂዎች በሰጡት ምላሽ ተመራቂዎች ሥራ አጥተው ለረጅም ጊዜ የመንከራተታቸው ዋና መንሴና ተጠያቂውም አንድና አንድ ነው ይሄውም የወያኔው አገዛዝ ነው:: ያሉብንን ችግሮች እንኩዋን ተነጋግረን መፍትሄ ለመፈለግ እንዳንረባረብ፣ ሃሳባችንን መግለጽ እንዳንችል ተቃውሞም እንዳናሰማ በተለያዩ ውስብስብ መንገዶች አፍኖን ይገኛል በማለት ገልጸዋል:: በመጨረሻም፣ ይህ አገዛዝ በወጣት ኢትዮጵያዊያን ላይ እየፈጸመ ያለው ግፍና በደል እንዲያበቃ የሚችሉትን ሁሉ ለማድረግ ቆርጠው መነሳታቸውን ገልጸው አስተያየታቸውን አጠናቀዋል።

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በንግዱ ማህበረሰብ ላይ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ገቢያቸውንና ወጪያቸውን በትክክል ለማሳወቅ ፍላጎት ካለማያሳየት የመጣ ነው፣ አገሪቱ የተያያዘችው የህዳሴ ጉዞም ግቡን ሊመታ የሚችለው ነጋዴው ግብር ሲከፍል ብቻ ነው በማለት ለመከራከር መሞከሩ ታውቁአል።

ይሁን እንጂ በስብሰባው የተካፈሉት የንግዱ ማህበረሰብ አካላት አገዛዙ ከገቢው ጋር ያልተመጣጠነ ፕሮጀክቶችን በመዝርጋቱ የሚፈጠርበትን የገንዘብ እጥረት ለመሸፈን ሲል ያልተመጣጠነ ግብር ይጥላል፣ ያለምንም ጥናት የሚጥለው ይሄው ግብር የንግዱን እንቅስቃሴ እያቀዘቀዘው ይገኛል በማለት አበክረው መናገራቸውን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጹአል። በዚሁ ስብሰባ ከነጋዴዎች ጋር የተደረገውን ውይይት ተከትሎ አገዛዙ ነጋዴዎች አምና ይከፍሉት የነበረውን ግብር አምነው እንዲከፍሉ ከዚያ ውጭ የተጠየቁትን እንዳይከፍሉ ሲል ትእዛዝ ማስተላለፉ ታውቁአል። ይህን ውሳኔ ተከትሎ የዘረኛው አገዛዝ ባለሙአል ያልተጠበቀ እርምጃ ያስገረማቸው ነጋዴዎች፣ ከዚህ ቀደም በግድ ከፈሉ ለተባሉት ግብር ማስያዣ የከፈሉት ገንዘብ እንዲመለስላቸውም መጠየቃቸው ታውቁአል።

ዘጋቢያችን የዚህን የግብር እዳ ስረዛ አስመልክቶ አስተያየት እንዲሰጡት የጠየቃቸው አንድ በአዲስ አበባ ከተማ የሚኖሩ ነጋዴ እንደተናገሩት፣ እኔ በህይወቴ እንደ ወያኔ ያለ ቀልደኛ አገዛዝ ገጥሞኝ አያውቅም፣ ውሳኔ ሲወስን በዘፈቀደ መሆኑ ሲያስገርመኝ፣ ይህኑ ውሳኔውን ሲሰርዝ ደግሞ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በግዴለሽነት ነው ብለዋል። ቀጥለውም ባለፈው ጊዜ በምግብ ሸቀጣሸቀጦች ላይ ድንገተኛ ውሳኔ አስተላለፈ፣ ይህ አልሳካ እንዳለ ሲረዳው ያለምንም ጥናት ውሳኔውን ሰረዘ:: እዚህ ላይ የሚገርመውና የሚያስደንቀው ነገር፣ ያኔ በምግብ ሸቀጦች ዋጋ ከጨመረ በሁአላ ውሳኔውን ሲሰርዝም ሆነ አሁንም በግብር ላይ ተመሳሳይ ድርጊትን ሲፈጽም ሁሉንም ነገር ያደረግሁት በጥናት ነው ማለቱ ነው በማለት አስተያየታቸውን አጠቃለዋል::

## ሪፖርተርስ ዊዝአውት ቦርደርስ የተባለው አለም አቀፍ የመብት ተሟጋች ድርጅት የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በስር ላይ የሚገኙ ጋዜጠኞችን እንዲፈታ ጠየቀ

ሪፖርተርስ ዊዝ አውት ቦርደርስ ለዘረኛው መለስ ዜናዊ በጻፈው ደብዳቤ ላይ እንዳመለከተው ካለፈው ሰኔ ወር ጀምሮ በእስር ላይ የሚገኙት ርእዮት አለሙና ውብሸት ታየ እስከፊ የእስር ጊዜ እያስተናገዱ ከመሆናቸውም በላይ ርእዮት አለሙ ጤናዋ አሳሳቢ መሆኑን፣ ውብሸት ደግሞ በእስርቤት ውስጥ ድብደባ እንደተፈጸመበት ገልጿል።

ሪፖርተርስ ዊዝ አውት ቦርደርስ በደብዳቤው ጋዜጣኛ ውብሸት ታየ በእስር ቤት ውስጥ የተፈጸመበት ጥቃትና ድብደባ በገለልተኛ ወገን ተጣርቶ አጥፊዎቹ ለፍርድ እንዲቀርቡም ጠይቋል።

ጋዜጠኛ ውብሸት ታየና ርእዮት አለሙ ካለፉት ሁለት ወራት ጀምረው በአሸባሪነት ተጠርጥረው በአሰቃቂነቱና በእሥረኞች ላይ በሚፈጸመው ሰቆቃ በአለም እውቅናን ባገኘው ማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ እንደሚገኙ ይታወቃል። ወያኔ እተዳደርበታለሁ በሚለው እና ተቃዋሚዎች እንዲያከብሩለት አጥብቆ በሚወተውተው ህገ መንግስት ተብዬ ሠነድ እስረኞች ምንም አይነት ሰብአዊ ክብራቸውን የሚጎዳ ሰቆቃ እንዳይፈጸምባቸው ፤ በቤተሰቦቻቸውና ጓደኞቻቸው እንዲጎበኙ፤ የህክምናና የህግ አገልግሎት እንዲያገኙ፤ የሚደነግግ ቢሆንም ወያኔ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በሌሎች እስረኞች ላይ ሲፈጽም የቆየው አይነት ሰቆቃ በሁለቱም ጋዜጠኞች ላይ እየደረሰ መሆኑን ጋዜጠኞቹ ፍርድ ቤት ለተባለው የወያኔ ተቋም ፊት ሲቀርቡ እንደተናገሩ ታውቆአል።

የአረቡን አለም አምባገነኖች እያተረማመሰ የሚገኘው አብዮት ከፈነዳ ወዲህ የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ከ300 ያላነሱ ኦሮሞዎችን ያለምንም ምክንያት አስሮ በ እስር ላይ እያሰቃየ እንደሚገኝ የታወቀ ሲሆን በአገራችን እየከፋ የመጣው የፖለቲካ አፈናና የኑሮ ውድነቱ እያሳከተለ ያለው ችግር የህዝቡን ብሶት እንደ ኢሳተ ጎሞራ ሳይታሰብ አንድ ቀን ሊያፈነዳው ይችላል የሚል ስጋት አገዛዙን እረፍት ነስቶታል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz
<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz
በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz
በ 49 MB በ 5980 KHz
እና በ 60 MB 4760 GHz

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ሰዓት በድጋሜም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን። <u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org